AEPAC
American Ethiopian Public Affairs Committee

**የዜና መዋእለ**

ሚያዝያ አንድ ቀን 2013 ዓ.ም
April 9, 2021

25ቀን2013 ዓም(April 3, 2021) በ"ዙም" ስብሰባአድርገው፤አዲስስለተቋቋመውናየአሜሪካኢትዮጵያዉያንሕዝብ ጉዳዮች አስፈጻሚ ኮሚቴ (አአፖአኮ) ወይም (American-Ethiopian Public Affairs Committee (AEPAC) ስለተሰኘው ድርጅት ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡ አአፓአኮ የፖለቲካ ጉዳዮች አራማጅ ኮሚቴ (Political Action Committee-PAC) በመባል ተሰይሞና፤ በአሜሪካ ተመዝግቦ፤ በህግ የተቋቋመና፤ በአሜሪካን የፌደራል መንግሥት የምርጫ ህግ፤ በፌደራል ምርጫ ኮሚሽን (Federal Election Commission-FEC) ስር የሚተዳደር ድርጅት ነው፡፡ አቶ መስፍን ተገኑ የድርጅቱ ሊቀመንበር፤ ለስብሰባዉ ተካፋዮች የድርጅቱን ተልእኮና ዓላማ እንደሚከተለው አስረድተዋል፡፡

**የእዚህ ፖለቲካ ጉዳዮች አራማጅ ኮሚቴ ዋና ዋና ዓላማወች፡**

- ታዋቂ የሕዝብ ግንኙነት ባለሚያ የግል ተቋም በመቅጠርና አብሮ በመሥራት፤ የኢትዮጵያን ስትራቴጂያዊ ጥቅሞች ለማስጠበቅ በሚደረጉት ጥረቶች ሁሉ ግንባር ቀደም መሪነት በመስጠት ማገልገል፤
- ጠንካራና ስኬታማ ተቋም በመሆን፤ በአሜሪካና ኢትዮጵያ መሀል ያለዉን ስትራቴጂያዊ ወዳጅነት እንዲጠናከር ተግቶ መሥራት፤
- ኢትዮጵያዉያን አሜሪካዉያን ተመዝግበው የመራጭነት መብታቸዉን በሁሉም ደረጃ፤ በፌደራል፤ በክፍለ ሀገርና በከተሞች ምርጫ በንቃት እንዲሳተፉ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፤
- ለፌደራል፤ ክፍለሀገርና ከተማ ቢሮወች በሕዝብ ለመመረጥ የሚወዳደሩትን ተመራጮች ከድርጅታችን አባላትና ደጋፊወች፤ ድጋፍ እንዲያገኙ ወይም እንዳያገኙ እንደሁኔታዉ መቀስቀስ፤
- ኢትዮጵያዉያን አሜሪካዉያን ለሕዝብ ምርጫ እንዲመዘገቡና እንዲወዳደሩ ማደፋፈርና መመልመል፤
- በ2022 እና 2024 (በፈረንጅ አቆጣጠር) ምርጫ፤ የኢትዮጵያ ወዳጆችና ደጋፊወች የሆኑ ለሴኔትና ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እስከ 10% ወይም በበለጠ መቀመጫ እንዲአሸንፉ በትጋት ቅስቀሳ ማካሄድ፤

በዚህ እለት፤ በስብሰባዉ የተገኙት በአሜሪካ፤ ካናዳና አዉሮፓ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ስቪክ ማህበራት ተወካዮች፤ ከአአፓአኮ አመራር ጋር በመተባበር፤ ጊዜአዊ የዓለም አቀፍ የሥራ አስተባባሪ ኮሚቴ (Ad Hoc Working Group) አቋቁመዋል፡፡ ይህ ኮሜቴ የተለያዩ ገንዘብ ማሰባሰብንና ሕዝብ ግንኙነትን ያካተቱ ተግባሮችን ያከናዉናል፤ ይህም ከላይ እንደተጠቀሰው፤ ዋናዉ ዓላማዉን የኢትዮጵያን ስትራቴጂያዊ ግቦችን ለማሟላት የሚያግዝ ሲሆን፤ ይህን ተግባር በተቀናጀ መልክ ለማስኬድ፤ ታዋቂና በቂ ችሎታ ያለው የሕዝብ ግንኙነት ተቋም ለመቅጠር ያስችላል፡፡

የስቪክ ማህበራት ተወካዮቹ፤ እንደዚሁም አባሎቻቸው አአፓአኮን በገንዘብ እርዳታ፤ በምክርና፤ ወዳጅነትን በማጠናከር በመሳሰሉት እንዲያግዙ እንደሚያበረታቱ ቃል ገብተዋል፡፡ ሁሉንም ኢትዮጵያዉያን አሜሪካዉያንና የኢትዮጵያ ወዳጆችንም አአፓአኮ የ2022 እና 2024 የአሜሪካ ምርጫ እቅዶቹንና አጀንዳወቹን በሥራ ላይ እንዲያዉል ሀገዝ እንደሚያበረክቱ ቃል ገብተዋል፡፡ ብዙወችም ከአሁኑ ቋሚ የገንዘብ እርዳታ ለመለገስ በድርጅቱ ድረገጽ ([https://aepact.org/](https://aepact.org/)) ተመዝግበዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለመላዉ እትዮጵያዊያን አሜሪካዉያን፤ በህጋዊ ፍቃድ አሜሪካ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን፤ ለሌሎችም ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችንና፤ በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ የኢትዮጵያ ወዳጆች በሙሉ ድርጅታችንን አአፓኮን እንዲደግፉና፤ ሀገራችንን ኢትዮጵያን ለመርዳት እንድንተባበር በአክብሮት ጥሪ እናቀርባለን፡፡

የአአፓአኮ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
ዋሽንግተን ዲሲ፣ ሚያዝያ 2 2013 ዓም (April 10, 2021)

## Representatives

| Name | Organisation |
|---|---|
| Mr. Abdelmaik | EDTF |
| Aklilu Demessie | EthiopiaWinNet - Council for the Defence Citizen Rights: E-CDCR Deputy to the Chief PR Officer |
| Dr. Araya Amsalu | Ethiopian Advocacy Network: ENA |
| Ato Beneyam Yinesu | Yetewled Delediy |
| Mr. Betru Gebere Ezigabeher | Global Alliance for Rights of Ethiopians |
| Bruck Tadesse | Worldwide Ethiopian Civic Associations Network: WE-CAN; Europe, Middle East and Africa (EMEA) Director |
| Ato Demilew Asfaw | Global Ethiopians Diaspora Society |
| Engineer EzkileEskinder | WE-CAN |
| | |
| Kone Feseha | Ethiopian Water Council: EWAC |
| Dr. Gebeyehu Ejigu | GERD support group |
| Ato Gebriel Negatu | Ethiopian Diaspora Communication Alliance |
| Dr. Haimanot | Ethiopian American Voters Registration |
| Ambassador Kassa Kebede | DMV Advocacy and Public Diplomacy |
| Ato Kitaw Yayehard | Ethiopian Advocacy Network in Switzerland (or Association) |
| Mr Konie | Ethiopian Water Council |
| Lidet Muleta | EDTF |
| Minilik Andarge | Worldwide Ethiopian Civic Associations Network: WE-CAN; Western US Region Director |
| Mr. Neamin Zeleke | GLEAN |
| Ato Samuel Habte | Ethiopian Dialogue Forum |
| Dr. Solomon | ECNAS |
| Tesfamichael Makonnen | EthiopiaWinNet- Council for the Defense Citizen Rights: E-CDCR |
| Dr. Tihut Assfaw | ECNAS |
| Yilma Zerihun | Vision Ethiopia: VE |
| Deacon Yosef Teferi | Ethiopian American Civic Council |
| Ms. Wassy Tesfa | GLEAN |
| Zeke Eskender | Worldwide Ethiopian Civic Associations Network: WE-CAN |
| Ato Zelalem Tessema | DEFEND Ethiopia UK APD |